# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 107 ግንቦት 26 ቀን 2002 ገጽ 1

**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ: "የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!:" የሚል ነው።**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ "እምቢ ለመብቴ!!!" ብቻ ነው**

## የምእራብ አገራት በኢትዮጵያ ባለው አገዛዝ ደስተኞች ናቸው ተባለ

ዘ ኢኮኖሚስት የተባለው ታዋቂ የእንግሊዝ መጽሔት ሰሞኑን ባወጣው ጽሁፍ፣ ምእራባውያን አገራት መረጋጋትን አስፍኗል በሚል በዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ደስተኞች ናቸው ብሏል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታየው ፍርሃት በ1970ዎቹ በሶቪየት ህብረት የኮሚኒስት አገዛዝ ስር ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች ፍርሃት ይመስላል ያለው ዘ ኢኮኖሚስት፤ እንደ ሶቭየት ህብረት በአጥር ባይከበቡም፣ የተቀረው አለም ዝምታ ግን የኢትዮጵያውያኑን ሁኔታ የከፋ አድርጎታል ብሏል።

እንደ ሶቭየት ህብረት ሁሉ በኢትዮጵያ ገዢውን ፓርቲ ለመቀላቀል ፈቃደኝነታቸውን የሚያሳዩት እድገት እና ሌላም ጥቅማ ጥቅም እንደሚሰጣቸው፤ እምቢ የሚሉት ደግሞ ያላቸውን እንደሚያጡ እና በአገዛዙ ላይ ጥያቄ የሚያነሱትን ደግሞ እስር እና ማስፈራራት እንደሚጠብቃቸው በመዘርዘር መጽሔቱ ኢትዮጵያውን ለረዥም ጊዜ ያወቁትን ሃቅ መስክሯል።

ይህ ሁሉ እየሆነ ግን ምእራባውያን አገራት በሰፊው ደስተኞች እንደሆኑ እና እንደ ዩጎዝላቪያው ቲቶ ያለ አመራር በኢትዮጵያ እንዲኖር ተስፋ እንደሚያደርጉ ጋዜጣው በጽሁፉ ገልጿል። ጆሲፕ ብሮዝ ቲቶ ዩጎዝላቪያን ለአስርተ አመታት የገዛ አምባገነን መሪ ሲሆን፤ በአመራር ዘመኑ ከፍተኛ አፈናን ማካሄዱ ይነገራል። እሱ እንደሞተም፣ መረጋጋትን አስፍኖባታል የተባለችው ዩጎዝላቪያ ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ዘቅጣ ታላቅ እልቂት ተከትሏል።

## በኢትዮጵያ የከተማ ውስጥ ድህነት መባባሱን እንደቀጠለ ታወቀ

የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ አገዛዝ እድገት በማምጣቴ ተመርጫለው እያለ በሚሳለቅበት ሰሞን፣ በአገሪቱ መዲና ችጋር መባባሱን እንደቀጠለ የሚያሳይ ዘገባ ለዝግጅት ክፍላችን ደርሷል።

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ህፃናት ከረሃብ የተነሳ በየትምህርት ቤቶች እራሳቸውን እየሳቱ እንደሚወድቁ የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከመዲናችን አጠናክሮ በላከው ዘገባ አሳውቋል። ዘጋቢያችን ከምስክሮች የደረሱትን ፍንጮች በመከተል ባደረገው ማጣራት፣ ይህ ችግር በመዲናይቱ ትምህርት ቤቶች የተስፋፋ እንደሆነ ለማወቅ ችሏል። ጉዳዩ ያሳሰባቸው መምህራን እና ሌሎች ግለሰቦችም የገንዘብ እርዳታ በማሰባሰብ ተማሪዎችን ለመመገብ ሙከራ ማድረግ መጀመራቸው ታውቋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ በየአመቱ እርዳታ የሚፈልጉ አስራ አራት ሚሊዮን የሚሆኑ ዜጎች ያሉ ሲሆን፤ አብዛኛው የእርዳታ ስራ የሚያተኩረውም በአርሶ አደሮች ላይ ነው።

ባለፉት በርካታ አመታት፤ በተለይም ወያኔ-ሰራሹ የዋጋ ንረት ከ97ቱ ምርጫ ወዲህ ከተፋፋመ በኋላ፣ የከተማ ውስጥ ድህነት ከዚህ ቀደም ታይቶ ወደማይታወቅ ደረጃ እየደረሰ መጥቷል። በርካታ ሰዎች ምግብ በተራ መብላት መጀመራቸውን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

## በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ የወያኔ ካድሬዎች በቂ ህዝብ እንዲመርጥ አላደረጋችሁም በሚል ግምገማ ተካሄደባቸው

በአዲስ አበባ በአንዳንድ ክፍለ ከተማዎች ያሉ የወያኔ ካድሬዎች በቂ ሰው ወደ ምርጫ እንዲወጣ፤ እንዲሁም ወያኔን እንዲመርጥ አላደረጋችሁም በሚል ግምገማ እንደተካሄደባቸው ታወቀ።

ባለፈው ሳምንት ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰን ፍንጭ በመከተል የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን እንዳረጋገጠው፥ በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ማግስት በየጣቢያው የተለጠፈው ውጤት ከታየ በኋላ ለወያኔ ተሰጠ የተባለው ድምጽ ቁጥር አርኪ ሆኖ ባለመገኘቱ ግምገማ ተደርጓል።

ከዚህ ቀደም ካድሬዎቹ ከቤት ቤት እየተዘዋወሩ ህዝቡ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ታሪክ በአለም ዙሪያ ያሉ ሴቶች ትግል ተምሳሌት ነው ተባለ

ሴቶች ለሴቶች የተባለው አለማቀፍ ግብረሰናይ ድርጅት ፕሬዚደንት እና የሴቶች መብት ተሚጋች የሆኑት አሜሪካዊት ወ/ሮ ዘይነብ ሳልቢ የወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ ታሪክ በአለም ዙሪያ ያሉ ሴቶች ትግል ተምሳሌት ነው አሉ።

ወ/ሮ ዘይነብ ብርትኳን ሚደቅሳ የህሊና እስረኛ ናቸው፤ የታሰሩትም አገዛዙን በመቃወማቸው ነው ብለዋል። ብርትኳን ሚደቅሳ የልጅ እናት እና የእናታቸው ጧሪም እንደመሆናቸው፤ መታሰራቸው ቤተሰባቸውን ችግር ላይ እንደጣለም ገልጸዋል።

ወ/ት ብርትኳን ከሶስት አመት በፊት በአሜሪካ ኮንግረስ ፊት ለምስክርነት ቀርበው ባደረጉት ንግግር፣ "ሰላምና መረጋጋት ሊገኝ የሚቻለው በውይይት እና በድርድር ብቻ ነው" ማለታቸውን አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ ካለው የመብት ረገጣና አፈና አኳያ እንደ ብርትኳን ያሉ ሰላማዊ ሰዎች እርቅና ሰላም ለማምጣት አስፈላጊ ሆነው ሳለ ያንን ከማድረግ መታገዳቸውን አውግዘዋል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወደ ኢትዮጵያ ስርጭቱን የጀመረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ታፍኖ እንደነበር ታወቀ

በቅርቡ የተመሰረተውና በአጭር ጊዜ ውስጥ ታዋቂነትን ያተረፈው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት ግንቦት 21 ቀን ባወጣው መግለጫ ከግንቦት 19 ቀን ጀምሮ ስርጭቱ ለአራት ተከታታይ ቀናት ተቋርጦ እንደነበር አስታውቋል።

በምህጻረ ቃል ኢሳት በመባል የሚታወቀው ቴሌቪዥን ጣቢያ፣ የሳተላይት አገልግሎት ከሚያቀርብለት ኩባንያ ባገኘው ማብራሪያ መሰረት ስርጭቱ ተቋረጦ የነበረበት ምክንያት፤ ምንጩ በውል ካልታወቀ አካባቢ በሚሰራጭ ሞገድ ኢላማ ተደርጎ እየተጠቃ በመሆኑ እንደሆነ ገልጿል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ዝግጅት ክፍል ከአስር ቀናት በፊት በደረሰው መረጃ፤ መለስ ዜናዊ በቢሮው አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ኢሳትን ማስቆም በሚችልበት መንገዶች ላይ ተወያይቷል። በወቅቱ የደረሰንን መረጃ ከሁለተኛ አካል ለማጣራት ባለመቻላችን ባናቀርበውም፤ እሁድ ግንቦት 22 ቀን ከመጀመሪያው ምንጫችን ጋር ግንኙነት ከሌለው ግለሰብ ከደረሰን መረጃ ጋር አመሳክረን ለማረጋገጥ ችለናል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር የነዳጅ ማእድን መስክ ተቆጣጥሬአለሁ አለ

የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ወይም ኦብነግ) ቅዳሜ ግንቦት 21 ቀን ባወጣው መግለጫ በሶማሌ ክልል የሚገኘውን የሂላል ነዳጅ ማእድን መስክ ተቆጣጥሬያለሁ ብሏል።

በቦታው ነዳጅ ሲያፈላልጉ የነበሩ የውጭ አገር ኩባንያዎች ስፍራውን ለቀው ቢሄዱም፣ የወያኔ ወታደሮች ግን ቀርተው እንደነበረ እና እነሱን አባሮ መስኩን መቆጣጠሩን ግንባሩ እንደገለጸ ብሉምበርግ የዜና አውታር ዘግቧል።

ጉዳዩን በሚመለከት ለሬውተርስ የዜና አገልግሎት መልስ የሰጠው የዘረኛው አገዛዝ ምክትል ዋሾ በረከት ስምኦን፥ መግለጫው ፍጹም ሃሰት እንደሆነና ኦብነግም ከስፍራው ከዚህ ቀደም ፈጽሞ መባረሩን ተናግሯል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የኦጋዴንን ህዝብ ለወራት ስቃይ ከዳረገ በኋላ ኦብነግን አጥፍቻለሁ ማለቱ ቢታወቅም፤ ከዛ በኋላ ግን በተደጋጋሚ ግንባሩ ያደረሰበትን ጥቃት ለማመን መገደዱ ይታወሳል። ከጥቂት ሳምንታት በፊት ኦብነግ በርካታ ወታደሮችን በመግደል አንድ ከተማ መቆጣጠሩን ሲናገር፤ የበረከት ምክትል ሽመልስ ከማል በሰጠው መግለጫ ውጊያ መከሰቱን ማመኑ ይታወሳል።

የተለያዩ የውጭ አገር ኩባንያዎች ሂላላ እና ካሉብ በተባሉት ቦታዎች የነዳጅ ማእድን በመፈለግ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን፤ ፔትሮናስ የተባለው የማሌዥያ ድርጅት ከሶስት አመታት በፊት ፍቃድ ለማግኘት ለወያኔ 80 ሚሊዮን ዶላር መክፈሉ በወቅቱ ተዘግቧል።

## ምርጫ ተሰደበ!!!

ምርጫ ተሰበደ፤ ተዋረደ። ምርጫ ዘንድሮ - በ2002ዓ.ም. - በኢትዮጵያ የደረሰበትን ያህል ውርደት የትም አገር ደርሶበት አያውቅም። ኧረ እንዲያውም እንዲህ ዓይነት ምርጫ የለም!!! የገዛ እራሱን እንዲያሸንፍ የተደረገ፤ ራሱን በራሱ ያስጠላ፤ የገዛ ራሱን ያዋረደ ምርጫ ምን ተብሎ ይጠራል? የዘንድሮው ምርጫ የምናውቀው ዓይነት አይደለም፤ እናም ስም የለውም።

አምባገነኖች በጉልበት የያዙትን ሥልጣን ህጋዊ ለማስመሰል የይስሙላ ምርጫን መፈለጋቸው የተለመደ ነው። ስለዚህም ወያኔን በጉልበት የያዘውን ሥልጣን ህጋዊ ለማስመሰል ምርጫን ተጠቅሞ ቢሆን ኖሮ ፈጽሞ ባልገረመን። እስካሁን "ምርጫ" እያለ ሲጠራቸው የነበሩ ድራማዎችዎችም የዚሁ ዓይነት ናቸው። የአሁኑ ግን ይለያል።

አንድ አምባገነን በጉልበት የያዘው ሥልጣን ህጋዊ አለመሆኑን ለማሳየት ምርጫን ሲጠቀም የዘንድሮው የመጀመሪያ ነው። ቀድሞዉኑ አንድ አምባገነን በጉልበት የያዘው ሥልጣን ህጋዊ አለመሆኑን መንገር ምን ያደርግለታል? የሚያደርግለት ነገር ካለስ እንደምን ምርጫን ለዚህ ተግባር ያውላል። "ምርጫ 2002" ወለፈንዲ የሆነብን ለዚህ ነው።

ወያኔ የቀድሞዋን ሶቭየት ኅብረትና አልባኒያ ዓይነት ሥርዓቶችን እየገነባሁ ነው ብሎ በግልጽ ተናግሮ ቢሆን ኖሮ የእንዳሁኑ ዓይነት ሙሉ በሙሉ ማሸነፍና በማግሥቱም ሰልፍ ማስወጣት የምንጠብቀው በሆነ ነበር። ያም ቢሆን ግን ሁሌም መቶ በመቶ ማሸነፍ ያስፈልጋል እንጂ በሰባ በመቶ ወደ መቶ በመቶ መሸጋገር አይቻልም። በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ ግን በውስጡ የአልባኒያ ፍቅር ቢኖርበትም ቢያንስ በአደባባይ ያንን ሥርዓት ማድነቅ ከተወ ውሎ አድሯል። ብዙዎቻችን ወያኔ በዲሞክራሲ ስም እየማሉና እየተገዘቱ ከሚኖሩ የዘመናችን አምባገነንና ዘረኛ ሥርዓቶች አንዱ አድርገን ስንመድበው ኖረናል። በዚህ ምርጫ ያሳየው ባህርይ ግን የሚመደበት ቦታ ማግኘት አስቸግሯል።

እስካሁን የምናውቃቸውን የምርጫ ዓይነቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል - ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እና የሴራ ምርጫ።

ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ነፃና ፍትሃዊ ሲሆን የተደላደለ የፖለቲካ ሜዳ ተፈጥሮ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች ለሥልጣን የሚወዳደሩበት ነው። ምርጫው ነፃና ፍትሃዊ እንዲሆን ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ አካል ይመራዋል። የአስፈፃሚውንም ገለልተኝነት ገለልተኛ ታዛቢ፣ ገለልተኛ ሚዲያ እና መላው ማኅበረሰብ ይቆጣጠረዋል። የመንግሥት ወታደር፤ ፖሊስ፤ የፀጥታና እንዲሁም ሲቪል አስተዳደሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ውጭ ናቸው። የመንግሥት ሃብት አንድን ፓርቲ አሸናፊ ለማድረግ ወይም ለማዳከም አይውልም። ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ሕዝብ በነፃ ህሊናው ለመረጠው ድምፁን ሰጥቶ የአብዛኛው ሕዝብ ድምፅ ወሳኝ የሚሆንበት አሰራር ነው።

የሴራ ምርጫ ደግሞ አራትና አምስት አመት እየጠበቁና አስመሳይ ምርጫ በማካሄድ የአንድ ፓርቲ ወይም የአንድ ግለሰብ አገዛዝን በምርጫ ስም የህጋዊነት ልባስ የማለበስ ሥራ ነው። አምባገነኖች የሴራ ምርጫ እያደረጉ "ተመረጥን" ማለታቸው የተለመደ ሆኗል። ስለሆነም የሴራ ምርጫ "ጨዋታ"፣ "ድራማ" ወይም "ተውኔት" ተብሎ ይገለፃል። እነዚህ ቃላት የሚመረጡት ምርጫው የምር አለመሆኑን ለመግለጽ ነው። የሴራ ምርጫ በአስቂኝነት ከጦዘ "ቧልታይ ተውኔት" ተብሎ ሊከሸን ይችላል። እኛም ይኸንን ጉደኛ የ20002ቱ ስም አይታወቄ "ቧልታይ ተውኔት" ብለን ስንጠራው ከርመን ነበር። አሁን ግን መሳሳታችንን አወቅን። የምርጫው ውጤት ማንንም አላሳቀም!!! እናም ቧልት ሊሆን አይበቃም።

ወያኔ ከዚህ ምርጫ ምን ተጠቀመ? ምንም!!! እርግጥ ትዕቢቱን ለመላው ዓለም ይፋ አደረገ። ይህ ጥቅም ነው ይባል ይሆን? ያም ቢሆን እኛ ኢትዮጵያዊያን የመለስን ትዕቢተኛነት ድሮም እናውቅ ነበር። በምርጫው ቅስቀሳው ወቅት የመለስ ዜናዊ የግል ተሳትፎ በብልግና ቃላት የተሞላ የነበረ መሆኑ አሁን ከውጤቱ ጋር ስናየው ወያኔ ምን እንደፈለገ ማወቅ ፈጽሞ አስቸጋሪ ያደርገዋል።

አምባገነኖች ራሳቸውን ዲሞክራት ለማስመሰል የይስሙላ ምርጫ ያደርጋሉ። መለስ ደግሞ "የለየልኝ አምባገነን ነኝ" ለማለት የዘንድሮን ምርጫ ተብዬ ነገር አደረገ።

ለምርጫ 2002 ስም አይታወቄ ስም ማግኘት ተቸግረናል። ለመሆኑ ህገወጠነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርጫ ምን ይባላል? ስም ካላችሁ እንድታካፍሉን እንጠይቃለን። በ pr@ginbot7.org ይፃፉልን።

### መድረክ የግንቦት 15ቱን የምርጫ ተውኔት ውጤት እንደማይቀበል ገለጸ፤ ምርጫው በድጋሚ እንዲካሄድም ጥሪ አቀረበ

መድረክ ፓርቲ ግንቦት 18 ቀን ባወጣው መግለጫ፣ የግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ተቀባይነት እንደሌለው በማውገዝ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ጠየቀ።

ፓርቲው በዚህ መግለጫ፥ ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ አፈፃጸም አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሳይስተካከሉ ምርጫው መካሄዱን እና አገዛዙ የፖለቲካውን መድረክ ሙሉ ለሙሉ ለመቆጣጠር ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ተግባሮች ላይ ተሰማርቶ መቆየቱን ገልጿል። መድረክ ይህንን ቢገነዘብም በምርጫው እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ ሆኖ ችግሮችን በውይይትና በድርድር ለማስወገድ ጥረት ለማድረግ መወሰኑን፤ ሆኖም ይኸም ጥረት በአገዛዙ ዘንድ ባለመስተናገዱ የምርጫው አፈፃጸም ችግር ውስር እንደሚገባ መረዳቱን ገልጿል።

መድረክ ገዢው ፓርቲ እና የምርጫ ቦርድ ለሃቅ በሃቅ የማይሰሩና የማይንቀሳቀሱ የውሸት እና የአስመሳይ ተግባራት ተቋማት ስለመሆናቸው ለአንዴና ለሁሉም ተጋልጧል ብሏል። የወያኔ አገዛዝ ከምርጫው ተውኔት በፊትና በእለቱ የተለያዩ አፋኝ ተግባራትን ማካሄዱን መግለጫው ጠቅሶ፤ ከእለቱ በኋላ ስድስት የመድረክ አባላት በጥይት ተመትተው መቁሰላቸውን፤ ሁለት በጩቤ መወጋታቸውን፤ እንዲሁም አንድ ሰው በጥይት መገደሉን ገልጿል።

መድረክ ፓርቲ ግንቦት 15 ቀን የተከናወነው ክስተት "ምርጫ" ሳይሆን "ድራማ" ነው ብሎታል። ስለዚህም፥ በድጋሚ መካሄድ አለበት የሚል ጥብቅ አቋም እንዳለው ገልጿል።

በጉዳዩ ላይ አስተያየት የጠየቅናቸው የግንቦት 7 ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፥ "የምርጫው ችግር በምርጫ እለት የተከሰተ፣ ከምርጫው በፊት ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎም የሆነ፣ በህገ-መንግስቱ ምርጫን በሚመለከት ከተጻፉት አንቀጾች ጋራ የተሳሰረ አይደለም። የምርጫዎቹ ችግር፣ ከወያኔ መሰረታዊ ጸረ-ኢትዮጵያዊነት እና ጸረ-ዴሞክራሲያዊነት የሚመነጭ ነው" ሲሉ ተደጋሚ ምርጫ ቢደረግ ምንም ለውጥ ያመጣል የሚል እምነት እንደሌላቸው ገልጸዋል።

አቶ አንዳርጋቸው፥ "ወያኔ በስልጣን ላይ ተቀምጦ እውነተኛ የህዝብ ፍላጎት የሚገለጽበት ምርጫ ይደረጋል ብሎ መገመት፣ ራስን ማታለል እና ስለወያኔ ማንነት በሚገባ የሚያውቀውን ህዝብ ለማታለል ከመሞከር ውጪ የሚፈይደው አንዳችም ነገር አይኖርም።" ብለዋል።

### የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች መሪ በምርጫው ተውኔት ላይ አሁን ካወጡት ይበልጥ የጠነከረ ሪፖርት ሊያወጡ ይችሉ እንደነበር ገለጹ

የታዛቢ ቡድኑ መሪ አቶ ታይስ በርማን የምርጫውን ተውኔት በሚመለከት አሁን ካወጡት በበለጠ የሚያወግዝ ሪፖርት ከማውጣት ሆን ብለው መቆጠባቸውን ብሉምበርግ የተባለው የዜና አውታር ዘገበ።

ቡድኑ ማክሰኞ እለት ባወጣው ሪፖርት የግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት አለም አቀፍ መስፈርቶችን እንደማያሟላ መግለጹን መዘገባችን ይታወሳል። አቶ ታይስ በርማን ለብሉምበርግ ዜና በሰጡት ቃል፥ ምርጫ ተብዬውን አሁን ካደረጉት በበለጠ ከማውገዝ የተቆጠቡበት ብቸኛው ምክንያት የኢትዮጵያው አገዛዝ አውሮፓ ለኢትዮጵያ ለምትሰጠው እርዳታ በሩን እንዳይዘጋ ስለሰጉ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜና፥ አቶ በርማን በወያኔ ቁጥጥር ስር ለሚገኘው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት በላኩት ደብዳቤ፤ ኢትዮጵያን ሄራልድ የተባለው ጋዜጣ ቡድናቸው የሰጠውን መግለጫ ሃሳብ በትክክል አለማቅረቡን አውግዘዋል። ጋዜጣው፥ "የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልኡክ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ብቁ፣ ብሔራዊ ምርጫውን ለማስፈጸም ሞያዊ ብቃት ያለው ነው አለ" በሚል ርእስ ባወጣው ጽሁፍ የታዛቢ ቡድኑ የምርጫውን ተውኔት እንዳሞጋገሰ አድርጎ ለማሳየት መሞከሩ ታውቋል። አቶ በርማን በደብዳቤያቸው፥ በሪፖርታቸው ውስጥ ስለምርጫው ተውኔት ያነሷቸው ቅሬታዎች በጋዜጣው ዘገባ ውስጥ አለመካተታቸው እንዳሳዘናቸው ገልጸዋል።

### የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ታሪክ በአለም . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለሰላማዊ ድርድር የቀረቡትን የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላት ሲያስር እና ለስደት ሲዳርግ መቆየቱ ይታወቃል።

ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ ላለፉት አስራ ሰባት ወራት እስር ቤት መቆየታቸው የሚታወስ ሲሆን፤ ከወላጅ እናታቸው እና ከህጻን ልጃቸው በስተቀር፣ ከሳቸው ወገን የሆነ ወይም ገለልተኛ አካል እንዲጎበኛቸው አይፈቀድም። ጤንነታቸው ስለመዛባቱ ዘገባዎች ቢወጡም፣ ሃኪም እንዲያዩ ግን አገዛዙ እንደማይፈቅድ ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

## የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎምዝ በዋሽንግተን ዲስ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቭዥን በተደረ የገንዘብ ማሰባሰብ ዝግጅት ያደረጉት ንግግር ግንቦት 15 2002 ዓ.ም (ክፍል 2)

ማንስ ያንን ጭፍጨፋ ያየ ሳያዝን ሊቀር ይቻለዋልን? ጭፍጨፋውን የሚያወግዝ መግለጫ ላወጣ እንደሆነ ስነግረው ሚኒስትር በረከት ስምኦን ለጭፍጨፋው ምክንያት የሆነው የአውሮጳ ህብረት አወጣ የተባለው ርፖርት ነው አለኝ። እኔም መለስኩና ህዝቡን የጨፈጨፈው እኛ የጻፍነው ወረቀት አይደለም ። ህዝቡን የጨፈጨፈው ያንተ ወታደሮች ያንተ ታጣቂዎች በአንተ በራስህ መሳሪያ ነው የጨፈጨፉዋቸው አልኩት። የሆነውን ሁሉ የምታውቁት ነው።

ይህንን ሁሉ ነገር እንዳስታውስ የሚያደርገኝ ምክንያት እነዚያ ቀናቶች ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ግሩም የሆኑ ትዝታዎችን ስለሚያስታውሰኝ ነው። አሁን ላይ ሆኜ ወደ ሁዋላ ስመለከት ይሄ ሁሉ ነገረ እንዲለወጡና ህዝቡ በነቂስ ከዳር እስከዳር ወጥቶ እንዲመርጥ ያደረገው ከምን በላይ ገዢው ፓርቲ የሰራው ትልቅ ስህተት ነው። ምክንያቱም ገዢው ፓርቲ እራሱን በህዝቡ ዘንድ ከፍ ያለ ተቀባይነት አለኝ ብሎ በመገመቱ እና በሌሌ በኩል ደግሞ ተቃዋሚው በህዝቡ አይን ድጋፍ እንደሌለው አድርጎ በመገመቱ በቀጥታ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ስርጭት አማካኝነት የተደረገውን የምርጫ ክርክር ከተለመደው ሳንሱር ነፃ በማድረግ ለተቃዋሚው በመፍቀዱ ነው። ይሄም ክርክር መደረጉ ይመስለኛል ህዝቡን የሳበው። ህዝቡ ለመጀመሪያ ግዜ ከተቃዋሚው ወገን ስላገሪቱ ችግሮች ግልጽ በሆነ መንገድ በብዛት በመስማቱ ነው ። ይህም ነው የ1997ቱን ምርጫ የተለየ ያደረገው።

አስታውሳለሁ ከምርጫው ቀደም ባሉት ቀናቶች ወደ ጎንደር፣ ሐረር እና ናዝሬት ሄጄ ነበር። በነዚህ ቦታዎች ሁሉ መንገድ ላይ ድንገት ያገኝሁዋቸህውን ሰዎች መኪና እያቆምኩ አነጋግሬአሉ። መለስ ዜናዊ የማደርገውን ነገር ሁሉ ሲቆጣጠር የነበረ መሆኑን ባውቅም በየቦታው ሄጄ መንገድ ላይ ድንገት እያቆምኩ ሰዎችን ማናገሬን ሊቆጣጠር ግን አልቻለም። ለምሳሌ ከብት ጠባቂዎችን አግኝቼ ማናገሬን ማስቆም አልቻለም። እነዚህን ጥያቄዎች ያገኝሁዋቸወን ሰዎች ሁሉ እጠይቅ ነበር። “ድምጽ የምትሰጡበት ጣቢያ የት እንደሆነ ታውቃላችሁ”?፣”ምን ማድረግ እንዳለባችሁስ ታውቃላችሁ”? ለሚሉት ጥያቄዎች በሙሉ መልሳቸው በሙሉ እናውቃለን ነበር። ሆኖም ግን ድምጻቸውን ለማን እንደሚሰጡ ልጠይቃቸው አልችልም። ነገር ግን ስለምርጫው በደንብ ግንዛቤ ነበራቸው። በ አስተርጉዋሚዬ በኩል ደጋግመው የሚያነሱት ጉዳይ በምርጫው ዘመቻ ወቅት የተደረገውን ክርክር መከታተል መቻላቸውን እና ያም ትልቅ ለውጥ እነዳመጣ ገልፀውልኛል። ልገልጽላችሁ የምወደው አንድ ነገር ቢኖር እዚህ ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ የማየው ሰው ወዳጄ ብርሃኑ ነጋ እውነተኛ ለውጥ እንዲመጣ በምርጫው ክርክር ግዜ ትልቅ ስራ ሰርቱዋል። በየቦታው በሄድንባቸው እና ህዝብ ባነጋገርንባቸው ቦታዎች ሁሉ በ አዲስ አ በባ ከተማ ጎዳናዎች ይሁን በሌሎች ከተሞች ወይም ወደ ጋራ ጥግ በሚወስዱ መንገዶች ላይ ያገኘናቸው ሰዎች ሁሉ የሱን ስም ነበር የሚጠሩልን። ምክንያቱም በክርክሩ ወቅት የተናገራቸውን ነገሮች ሁሉ ሳንሱር ሳይደረጉ ስላዳመጡት ነበር። ይህን ሁሉ መፍቀዱ ታዲያ ትልቅ ስህተት እንደነበር ስለተገነዘበ መለስ ዜናዊ ይህንን ስህተት መድገም አልፈለገም።

በመሆኑም በ አሁኑ ምርጫ ወቅት በቴሌቪዥን እና በሬዲዮ በቀጥታ የሚተላለፍ ክርክር አልተፈቀደም። መገናኛ ብዙሃን ከምንግዜውም በበለጠ በገዢው ቡድን ቁጥጥር ስር ወድቀዋል። የመብት አፈናው በ እጅጉ ተስፋፍቱዋል። ሰሞኑን እየደረሱ ስላሉት የመብት ረገጣ የሚወጡትን ዘገባዎች ሁላችንም እናውቃለን። ይህ አገዛዝ እኮ የ አሜሪካን ድምጽ ሬዲዮን እና የጀርመን ድምጽን ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝብ እንዳይሰማቸው አፍኛለሁ ብሎ የሚኩራራ ነው። እንዴት ነው ይህ አገዛዝ ይህንን ሁሉ አፈና በ ኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሲያደርስ የ አሜሪካ እና የ አውሮጳ አገራት መሪዎች እንዳልሰማ እንዳላየ ሊሆኑ የሚችሉት? አንድ ነገር ልንገራችሁ። አሁን ያለምዘውድ ከጥቂት ወራት በፊት ከተናገርኩት ውስጥ እንደጠቀሰችው የዘንድሮው ምርጫ ድራማ እንደሚሆንና የ አውሮጳ የምርጫ ታዛቢዎችም ያንን ድራማ ለመታዘብ እዚያ መገኘታቸው ለ አገዛዙ እውቅና መስጠት ይሆናል የሚል ፍርሃት አለኝ። የሚያስገርመው እኛ በ1997ቱ ምርጫ ወቅት ስለታዘብነው በመረጃ የተደገፈ ጠንካራ ሪፖርት ካወጣን በሁዋላ ያንን ሁሉ የደረሰውን ወደጎን በመተው እናም እያወቁ የ አውሮጳ ህብረት በዚህ ጊዜ ታዛቢ ለመላክ መወሰኑ ነው። ከጥቂት ቀናት በፊት መንግስት የ1997ዩን ምርጫ አሸንፉዋል ብሎ ቶኒ ብሌር የሰጠውን ንግግር አንብቤ ነበር ። እንዴት እንዲህ ሊል ይችላል? እኛ የ አውሮጳ የምርጫ ታዛቢዎች ይህንን አላልንም እስከ አሁኑዋም ቀን ድረስ በትክክል ማን እንዳሸነፈ የሚታወቅ ነገር የለም። የካርተር ሴንተርም ቢሆን ሪፖርቱን ከአምስት አመት በሁዋላ ቢሆንም ያወጣው መንግስት አሸንፉዋል አላለም። ቢዘገይም ግን ሪፖረቱን በመጨረሻ ይፋ ማድረጉ እሰየው ያስብላል።

ይሔ ሁሉ ሲሆን ግን አንድ ሁላችንም የምናውቀው ግልጽ የሆነው ነገር ዲስ አ በባ ላይ ተቃዋሚው ሙሉ ለሙሉ 23ቱንም መቀመጫ ማሸነፉን ነው። የምናውቀው ነገር ቢኖር ማሰባሰብ በቻልነው ናሙና መረጃ መሰረት በሁሉም ክርሎች ትግራይንም ጨምሮ ተቃዋሚዎች ከፍተኛውን ውጤት እንዳስቆጠሩ ነው። ታዲያ እውነታው ይህ በሆነበት ሁኔታ ቶኒ ብሌር ከየት አምጥቶ ነው መንግስት ነው ምርጫውን ያሸነፈው ሊል የቻለው? እኛም ሆንን ከ አምስት አመት በሁዋላ ዘግይቶ በወጣው ሪፖርቱ የካርተር ሴንተር ይህን አላልንም። እኔም ሆንኩኝ እናንተ እነዚህ የአውሮጳ አገራት መሪዎች ስለዚህ ምርጫ የሆነውን ሁሉ በግልጽ የሚያስቀምጥ ማስረጃ የአውሮጳ ህብረት ታዛቢዎች አደራጅተን ያወጣነውን ሪፖርት ማስረጃዎቹን እየተመለከቱ ይህንን ሸፍጥ የተሞላበት ስራ የሚሰሩት ለምን እንደሆነ በሌላ በኩል ደግሞ ለምን እንደሚያደርጉት በደንብ የምናውቀው ነገርም አለ።

ወዳጆቼ እኔ ይሄን ሁሉ ስል ስለዚህ ምርጫ የታዘብኩትን የራሴን አመለካከት ብቻ እያስተጋባሁ እንዳልሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ። እያስተጋባሁት ያለሁት ሁለት መቶ የሚሆኑት ከኔ ጋራ የ1997ቱን የ ኢትዮጵያን ምርጫ ለመታዘብ የመጡትን ያውሮጳ ህብረት ታዛቢዎች የእያንዳንዳቸውንም ሀሳብ ጭምር ነው። እነዚህ ባልደረቦቼ የብዙ ግዜ የምርጫ መታዘብ ልምድ ያካበቱ ናቸው። በ አለም ዙሪያ ሁሉ በመሄድ ብዙ ምርጫዎችን የታዘቡ ናቸው። እያንዳንዳቸው የእኔን ለእውነት መቆምና ስለምርጫው እነሱም እንደታዘቡት ሁሉ እውነቱን መናገሬን ደግፈዋል። በምንም ተአምር የሚደረግብኝን ጫና ሁሉ ተቋቁሜ እውነታውን እንደይሸፋፈን እና እውነታውን እስከመጨረሻው ይዤ በ አቋዋሜ እንድጸና በጣም ደግፈውኛል።

አሁንም ድረስ ሊገባኝ ያልቻለው ነገር ግን እኛም እነሱም ሁላችንም አሳምረን እንደምናውቀው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የለየለት አፋኝ አምባገነን መንግስት መሆኑን እያወቁ ለ እሱ አገዛዝ እውቅናን መስጠት መቀጠላቸው ነው ሁኔታውን ሁሉ በ እውነት አሳዛኝ የሚያደርገው። እውነታው ይህ አፋኝ አገዛዝ ኢትዮጵያን እና ህዝቡዋን ወደ ልማት እና መልካም አስተዳደር ጎዳና እንደማይመራት ይልቁንም እንደ አሻው በሚዘውረው የእድገት ስታቲስቲክስ ሆነ እንደፈለገው በሚያጭበረብረው የምርጫ ውጤት አገሪቱዋን አደህይቶ ህዝቡዋንም ረግጦ እና አፍኖ የሚገዛ መሆኑን በደንብ ያውቃሉ እኛም እናውቃለን።

ይህ ሁሉ እየታወቀ ታዲያ እንዳላዩ እና እንዳልሰሙ የማስመሰሉ አዝማሚያ በጠንካራ ማስረጃ ተደግፈው እኛም በአይናችን ጭምር ያየናቸውን አገዛዙ የሚፈጽማቸውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የህዝብን ድምጽ መስረቅን እና አጠቃላይ ምርጫን ማጭበርበር የመሳሰሉ ወንጀሎችን አይቶ እንዳላየ በመምሰል እራስን ከመሸንገል ያለፈ ጉዳይ አይደለም።

ይህ ሁሉ እራስን መሸንገል ያስፈለገው ለምን እንደሆነ ሲጠየቁ በ አብዛኛው ግዜ የምእራባውያን መንግስታት በምክንያትነት ከሚየቀርቡት መካከል አስቂኙ እና አሳዛኙ ኢትዮጵያ ቀውስ ውስጥ እንድትገባ እና እንድትበታተን መፍቀድ የለብንም የሚሉት ፈሊጥ ነው።

ለኔ ይሄ አመለካከት እብሪት የተሞላበት ነው። ኢትዮጵያ የስልጣኔ ምንጭ የሆነች እና ለዘመናት ህዝቡዋ አብሮ በሰላም የኖረባት አገር ናት። ኢትዮጵያ ቀደምት ስልጣኔ የነበራት አገር በመሆኑዋም በቅኝ አገዛዝ ስር ሳትወድቅ ነጻነቱዋን ጠብቃ የኖረች ናት። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ብሄረሰቦቹዋ በልዩነታቸውም ውስጥ በአንድነት መኖር የቻሉባት አገር ናት።

ታዲያ አውሮጳውያንም ሆኑ ሌሎች የውጪ ሀይሎች እንዴት ብለው ነው ይህችን እራሱዋን ችላ ስታስተዳድር የኖረችን አገር አንዱን ቡድን ከሌላው ቡድን በመምረጥ አገሪቱዋን ከመበታተን የምናድናት የሚሉን። ለምሳሌ ይህንን አመለካከታቸውን ጎረቤት በሆነችው ሱዳን ላይ ሲያራምዱ አላይም። በግልጽ እንደሚታየው ደቡብ ሱዳን እንድትገነጠል የምእራብ አገሮች ጣልቃ በመግባት ግፊት እያደረጉ እንዳለ እናያለን። ይሄን የሚያደርጉት ታዲያ ደቡብ ሱዳን በሰሜን ሱዳን በሚመራው አገዛዝ የሚደርስባቸውን አፈና ተማረው በ የግዜው ድምጻቸውን እያሰሙም ነው። ለዚህ የተለያየ አመለካከት ምክንያቱ ታዲያ በጣም ግልጽ ነው። በሱዳን ውስጥ የሚገኝ ነገር ግን ኢትዮጵያ ለጊዜው የሌላት ነገር ነው። ነዳጅ! ይህ ነው ዋናው ምክንያቱ። መሰነጣጠቁ ለሱዳን ሲበጅ ለኢትዮጵያ ጥሩ እንዳልሆነ ይሰብኩናል።

ሌላው የእብሪት አመለካከት ደግሞ ይህ የመለስ አፋኝ አገዛዝ የአገሪቱዋን አንድነት አስጠብቆ እኛ በአሸባሪዎች እና የተለያየ ስም እየሰጡ በምናባቸው በሚፈጥሩዋቸው ቡድኖች ላይ ከፊትነው ለሚሉት ዘመቻ አጋዥ ነው ብለው እስከቆጠሩት ድረስ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰትም ሆነ የህግ ልእልና አለመከበር እንዳላየ ሆነን ማለፍ እንችላለን የሚባለው ነው።

ይህ አስደንጋጭና አሳፋሪ አመለካከት የሚመነጨው ከእብሪት እና እኔ እንደውም ከዘረኝነት አመለካከት የመጣ ነው እስከማለት ደርሻለሁ። የ ኢትዮጵያ ህዝብ ለምሳሌ እኛ በአውሮጳ የምንኖር ሰዎች ያለንን መብትና ዴሞክራሲ እነ እርሱ እንፈልጋልነ እስካሉ ድረስ ሊያገኙ አይገባቸውም ? ደግሞም እነዚህን መብቶቻቸው እንዲከበሩላቸው እንደሚፈልጉም እኔ በ1997ት ምርጫ ወቅት ከህዝቡ ፊትም ላይ አይቻለሁ፣ ያነጋገርኩዋቸውም ሰዎች ይህንኑ ነው የገለጹልኝ እኔም በገዛ አይኔ ተመልክቼዋለሁ። ልክ እዚህ አሜሪካን አገር እና አውሮጳ ውስጥ የምትኖሩት ኢትዮጵያውያን ያላችሁን አይነት መብት ኢትዮጵያውያኖችም የሚፈልጉት እሱን እና ልማት፣ ስራ እንዲሁም ለልጆቻቸው የወደፊት እድል ለመፍጠር ነው። እዚህ ያላችሁት ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ዘመዶቻችሁ ጋር የተቆራኘ ግንኙነት እንዳላችሁ ሁሉ እናንተ ለነዚህ ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር እና ተጠቃሚ ለመሆን ዝግጁ የሆናችሁትን ያህል እነዚያም ቤተሰቦቻችሁ እንዲሁ ዝግጁዎች ናቸው። . . . (ክፍል 3 ሳምንት ይቀርባል)

## በግንቦት 15ቱ የምርጫ ተውኔት ላይ የሚደረጉ ውግዘቶች እንደቀጠሉ ነው

የእሁዱን የምርጫ ተውኔት በሚመለከት በተለያዩ የመረጃ አውታሮች የተሰጡ አስተያየቶች፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አፈና በደርግ ጊዜ ወደ ነበረበት ደረጃ መመለሱ እንደተረጋገጠ እየገለጹ ነው።

የአሜሪካ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም ኮንግረስ አባል የሆኑት ኤድ ሮይስ "ተጨማሪ አስራ ዘጠኝ አመታት ለመለስ ዜናዊ" በሚል ርእስ ባወጡት ጽሁፋቸው፤ "የመለስ አገዛዝ የአፈናውን ነገር በደምብ የሰለጠነበት ይመስላል" ብለዋል። ሮቤሌ አባ ቢያ የተባሉ የፖለቲካ ተንታኝ ደግሞ "የኢትዮጵያ ዴሞክርሲ በአስርተ አመታት ወደ ኋላ መመለስ" በሚል ርእስ፤ መለስ ዜናዊ 99.6% መቀመጫ አሸንፍኩኝ በማለቱ ከሱ ቀድሞ የነበረውን አምባገነን መንግስቱ ሃይለማርያምን እንኳ መብለጡን ተናግረዋል።

ፊላዴልፊያ ኢንኳየረር የተባለው የአሜሪካን አገር ጋዜጣ፣ ሐሙስ እለት ባወጣው ርእሰ አንቀጹ፣ "የኢትዮጵያ እጣ ከአንድ አምባገነን ወደ ሌላ ሆኗል" ሲል፤ የኬንያው ደይሊ ኔሽን ደግሞ "ሽፍጥ የሆነው ምርጫ" በሚል ርእስ በወጣው ርእሰ አንቀጽ፣ መለስ ዜናዊ በአፍሪካ ከቀሩት ጥቂት አምባገነኖች አንዱ ሆኖ ሳለ ምእራባውያን ለምን ዝም እንደሚሉት ጥያቄ እያስነሳ ነው ብሏል።

አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው የዜና አውታር በበኩሉ መለስ አሸነፍኩት የሚለው የፓርላማ መቀመጫ ፐርሰንቴጅ የአፍሪካን ሬኮርድ መስበሩን ተንትኗል።

ከነዚህም በተጨማሪ በርካታ ጽሁፎች ኢትዮጵያን የአንድ-ፓርቲ አገር ሲሉ የገለጹ ሲሆን፤ አገዛዙን ደግሞ አፋኝ ሲሉ አውግዘዋል።

## ወደ ኢትዮጵያ ስርጭቱን የጀመረው የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መለስ ዜናዊ በጠራው በዚህ ስብሰባ ላይ የውጭ አገር አማካሪዎች ጭምር የነበሩ ሲሆን፤ ኢሳትን ለማስቆም በዋነኛነት ሶስት አማራጮች ተነስተው ነበር። አንዱ በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን የሳተላይት ዲሾች ሁሉ መሰብሰብ የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በሳተላይት ዲሽ ባለቤቶች ላይ ተጨማሪ ግብር መጣል የሚል ነበር። ነገር ግን እነዚህ ሃሳቦች በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜው በስራ ላይ ሊውሉ አይችሉም ተብሎ ሶስተኛው ሃሳብ ላይ ተረግቷል። ይህም ሃሳብ ዘላቂ መፍትሄ እስኪገኝ ድረስ ለጊዜው የቴሌቪዥን ድርጅቱ የሚያስተላልፋቸውን ዝግጅቶች ሁሉ በመቅዳት የሚያስከስስ ምክንያት መፈለግ እና፤ ድርጅቱን በውጭ አገር በክስ በማጣደፍ የሚከፍለው እንዲያጣ አድርጎ ማስዘጋት የሚል ነበር።

የዝግጅት ክፍላችን ጉዳዩን በሚመለከት ያናገራቸው በርካታ ግለሰቦች ከስርጭቱ መቋረጥ በስተጀርባ የወያኔ እጅ እንዳለበት ያምናሉ። የአሜሪካ ድምጽ ራድዮ በተለያዩ ጊዜያት ጃሚንግ ወይም አፈና ሲፈጸምበት ቆይቶ ከጥቂት ወራት በፊት መለስ ዜናዊ እራሱ አገዛዙ እንዳፈነው ማመኑ ይታወሳል። አገዛዙ የኢሳትን ስርጭት ለማስቆም ፍላጎት ማሳየቱ የተረጋገጠ ቢሆንም፤ በሳተላይት የሚተላለፍን የቴሌቪዥን ስርጭት ለማፈን የሚያስችለውን ውድ ቴክኖሎጂ ግን አለው ተብሎ አይታመንም።

በዚህም ምክንያት ወያኔ አሁን በኢሳት ስርጭት ላይ የተካሄደውን አፈና ለማስፈጽም እጅግ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እንዳፈሰሰ ይገመታል። ይህም በውጭ ምንዛሬ የሚደረግ ወጪ እንደመሆኑ፤ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች በእርዳታ የመጣ ገንዘብ አሁንም ለሌላ እኩይ ተግባር የመዋሉ ማስረጃ ነው ይላሉ።

የቴሌቪዥኑ ስርጭት ተቋርጦ በነበረበት ወቅት በሺሆች የሚቆጠሩ የስልክና የኢ-ሜይል መልክቶች ከኢትዮጵያና ከተለያዩ የአለማችን ክፍሎች ለድርጅቱ መድረሳቸው ታውቋል። ኢሳት ባወጣው መግለጫ ተመልካቾቹና ደጋፊዎቹ ሁለንተናዊ ድጋፋቸውን እንዲለግሱት ጥሪ አቅርቦ የድርጅቱ አመራር የገባውን ቃል ኪዳን ለማሳካት የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም ብሏል።

## የአሜሪካ መንግስት ከዘረኛው የመለስ አገዛዝ ጋር ያለው ግንኙነት አደጋ ላይ ነው ሲል አስጠነቀቀ

የአሜሪካ መንግስት በሰጠው መግለጫ ከኢትዮጵያው አገዛዝ ጋር የሚኖረው የወደፊት ግንኙነት አገዛዙ የአለማቀፉ ማህበረሰብ የእሁዱን ምርጫ ተውኔት በሚመለከት ላቀረባቸው ሂሶች በሚሰጣቸው ምላሾች ላይ የተንተራሰ ይሆናል ሲል ማስጠንቀቁን የአሜሪካ ድምጽ ዘግቧል።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ የምርጫው ቅድመ ሁኔታ ለገዢው ፓርቲ ያደላ መሆኑን ተናግሯል። የኦባማ አስተዳደር አገዛዙ አሁን ያለውን ሁኔታ ለማሻሻል ግልጽ የሆኑ እርምጃዎችን ካልወሰደ የወደፊት ግንኙነታቸው አደጋ ላይ እምደሚሆን አስጠንቅቋል።

የእንግሊዝ መንግስትም ሐሙስ ግንቦት 19 ቀን ባወጣው መግለጫ የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድን ያወጣውን ሪፖርት ደግፏል።

ምንም እንኳን መንግስታቱ ከምርጫ 97 ጋር ሲወዳደር፣ በተለይም የአሜሪካኑ መንግስት፣ የወያኔን አምባገነናዊነት ከማመን ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው የተረዱ ቢመስሉም፤ የዝግጅት ክፍላችን ያናገራቸው ሁለት ኢትዮጵያውያን ምእራባውያኑ ተጨባጭ እርምጃ ይወስዳሉ የሚል እምነት እንደሌላቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

## በአዲስ አበባ ከተማ ያሉ የወያኔ ካድሬዎች

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ማንን እንደሚመርጥ በመጠየቅ ስም እና አድራሻ ሲጽፉ መቆየታቸው ይታወሳል። በዛ አኳኋን የሰበሰቡት እና በምርጫው ቀን የተገኘው ቁጥር ባለመግጠሙም ካድሬዎቹ ተቆጥተዋል።

ከግምገማው በኋላ በተደረገ ውሳኔም ወደየሰው ቤት በመሄድ ወያኔን አልመረጡም ብለው የሚገምቷቸውን እና ጭራሹን በምርጫ ያልተሳተፉትን ሰዎች በመለየት ማስፈራራት መጀመራቸው ታውቋል። ከምርጫው በፊት የፈጸሙላቸውን ውለታ እና የሰጧቸውን ቃል በማስታወስም ማስፈራራታቸውን ተያይዘውታል። አንዳንድ ካድሬዎችም፥ "የአዲስ አበባ ህዝብ እስካሁን አልተማረም ማለት ነው፤ ቆይ ዋጋውን ያገኛል" በሚል ሲዝቱ ተሰምተዋል።

የወያኔ ባለስልጣናት በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን በሰጧቸው መግለጫዎች እንዲህ አይነት ድል እንዳልጠበቁ በመናገር ቢዋሹም፤ ላለፉት አምስት አመታት በአገሪቱ ውስጥ እንዲንሰራፋ ያደረጉት አፋኝ የድርጅት መዋቅር ግን ከዚህ ያነሰ ውጤት እንዳልጠበቁ ያጋልጥባቸዋል። ከነዚህ መዋቅሮች ውስጥ አንዱም ህዝቡን እስከቤተሰብ ደረጃ ድረስ ወርዶ የሚቆጣጠር የአስተዳደር እና የፓርቲ መዋቅር መገንባት ነበር። እነዚህ ካድሬዎች አሁን እንዲገመገሙ የተደረገውም ያንን አፋኝ መዋቅር በተገቢው በስራ ላይ አላዋላችሁም በሚል ነው።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org